# በቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ዩኒቨርሲቲና ፡ በኖርዝዌስተርን ፡ ዩኒቨርሲቲ ፡ መተባበር ፡ የተደረገ ፡ ምርምር ።

## መግቢያ ፡

ኩዊንቲን ፡ ጆንስተን ፤

የሕግ ፡ ፕሮፌሰር ፤ ዬል ፡ ዩኒቨርሲቲ ፤ ቀድሞ ፡ በቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ዩኒቨርሲቲ ፡ የሕግ ፡ ዲንና ፡ ፕሮፌሰር ።

ሕግና ፡ የሕግ ፡ ድርጅቶች ፤ የሰውን ፡ ልጅ ፡ ጉዳዮች ፡ የተሻለ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት፡ ለማስያዝ ፡ የተፈጠሩ ፡ ዘዴዎች ፡ እንጅ ፤ እራሳቸው ፡ እንደ ፡ ግብ ፡ የሚቆጠሩ ፡ አይደሉም ። የአንድ ፡ ሕግ ፡ ዋጋ ፡ የሚመዘነው ፡ ያገለግላል ፡ ተብሎ ፡ በታሰበው ፡ በኅብረተሰብ ፡ ላይ ፡ በሚያመጣው ፡ ለውጥ ፡ ነው ። ውጤቱ ፡ ጠቃሚ ፡ ሆኖ ፡ ከተገኘ፤ ሕጉ ፡ ዋጋ ፡ የሚሰጠው ፡ ይሆናል ፤ ሕጉ ፡ ውጤት ፡ ያልሰጠ ፡ እንደሆን ፡ ወይም ፡ መጥፎ ፡ ውጤትን ፡ ካስከተለ ፤ ሕጉ ፡ ትርጉም ፡ የሌለው ፡ ወይም ፡ ከዚያ ፡ የባሰ ፡ ሆኖ፡ ሊገመትና ፤ መሻር ፡ ወይም ፡ አስተዳደሩ ፡ ፈጽሞ ፡ መለወጥ ፡ የሚያስፈልገው ፡ ይሆናል።

አንድ ፡ ሕግ ፡ በሁለት ፡ አገሮች ፡ ውስጥ ፡ ታውጆ ፤ በእያንዳንዱ ፡ አገር ፡ ውስጥ፡ ግን ፡ የሚያስከትለው ፡ ውጤት ፡ እጅግ ፡ የተለያየ ፡ ሊሆን ፡ ይችላል ። የቋንቋው ፡ አንድ ፡ መሆን ፤ አንድ ፡ ዓይነት ፡ ውጤትን ፡ እንዲያስከትል ፡ ማረጋገጫ ፡ ሊሆን ፡ አይችልም ። አንድ ፡ ሕግ ፡ የሚያስከትለው ፡ ውጤት ፡ እንደ ፡ ኅብረተ ፡ ሰቡ ፡ ዓይነት ፡ በጣም ፡ ሊለያዩ ፡ በሚችሉ ፤ እያሌ ፡ የባሕል ፡ ልዩነቶች ፡ ላይ ፡ የተመሠረተ ፡ ነው ። ስለልዩ ፡ ልዩ ፡ አገሮች ፡ ሕገ ፡ መንግሥቶች ፡ ከሚደረገው ፡ ጥናት ፤ ወይም ፡ ከውጭ፡ የመጡ ፡ ሕጐች ፡ ታሪክ ፡ ጋር ፡ የተላመደ ፡ ማንኛውም ፡ ሰው ፤ ይህን ፡ መሠረታዊ ፡ ፍሬ ፡ ነገር ፡ ጠንቅቆ ፡ ማወቅ ፡ ይገባዋል ።

ምንም ፡ እንኳ ፤ የተለያዩ ፡ ሰዎች ፡ ጥሩና ፡ መጥፎን ፡ ለመለየት ፡ የተለያዩ ፡ ሚዛን ፡ ቢኖራቸውና ፡ ከዚህም ፡ የተነሳ ፡ ስለአንድ ፡ ሕግ ፡ ጥቅምና ፡ ጉዳት ፡ የሚሰጡት ፡ መደምደሚያ ፡ አስተያየቶች ፡ ቢለያዩ ፤ አንድን ፡ ሕግ ፡ በቂ ፡ በሆነ ፡ አኳኋን ፡ ለማመዛዘን ፤ የዚያን ፡ ሕግ ፡ ውጤት ፡ ማወቅ ፡ ተቀዳሚ ፡ አስፈላጊ ፡ ነገር ፡ ነው ። በምን ፡ ላይ ፡ እንደሚጠቀሙበት ፡ ሳያውቁ ፤ የሞራልን ፡ ደንብ ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ ማዋል፡ የሚሰጠው ፡ ትርጉም ፡ እምብዛም ፡ ነው ።

የአንድን ፡ ሕግ ፡ ውጤት ፡ ለመገመት ፡ የሚያዳግት ፡ ከመሆኑም ፡ በላይ ፤ ኅብረተ ፡ ሰቡን ፡ በጣም ፡ የሚያውቁት ፡ በተለይም ፡ አንድ ፡ ሕግ ፡ ተፈጻሚ ፡ በሆነባቸው፡ የሥራ ፡ መስኮች ፡ ላይ ፡ የተሠማሩ ፡ ሰዎች ፡ የሚሰጡት ፡ ግምት ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ዋጋ ፡ ያለው ፡ ይሆናል ። ነገር ፡ ግን ፤ የውጤቱ ፡ ጥናት ፡ ቅንጅት ፡ ያለው ፡ ሆኖ ፡ በአጠቃ ላይ ፡ አኳኋን ፡ ከተደረገ ፤ የሚሰጠው ፡ አስተያየት ፡ የበለጠ ፡ ትክክለኛ ፡ ይሆናል ። እንዲሁም ፡ ተመራማሪዎቹ ፡ በግል ፡ ስሜታቸው ፡ ባይመሩ ፡ ለጥናቱ ፡ በጣም ፡ ይረዳል ። አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፤ በለሙትም ፡ ሆነ ፡ በታዳጊ ፡ አገሮች ፡ ውስጥ ፤ ነገሩን ፡ በትክክል ፡ ባለመመርመር ፡ በግል ፡ ስሜት ፡ ላይ ፡ መሠረተ ፡ አስተያየቶች ፡ የአንድን ፡ ሕግ ፡ ውጤት ፡ ለመመዘን ፡ እምነት ፡ የተጣለባቸው ፡ ምንጮች ፡ ናቸው ።

የአንድን ፡ ሕግ ፡ መውጣት ፡ ለመወሰን ፡ ይቻል ፡ ዘንድ ፤ በሥራ ፡ ላይ ፡ ሊውል ፡ የሚችል ፡ ሕግ ፡ የሌላውን ፡ የኅብረተ ፡ ሰቡን ፡ አንድ ፡ ክፍል ፡ የማጥናቱ ፡ ጉዳይ ፡

የሕግን ፡ ውጤት ፡ ከማጥናቱ ፡ ጉዳይ ፡ ጋር ፡ ተመሳሳይ ፡ ነው ። የሚያስፈልጉት ፡
ነገሮች ፡ ምን ፡ ምን ፡ እንደሆኑ ፡ ለመወሰን ፡ የሚረዱት ፡ ፍሬ ፡ ነገሮች ፡ ከተተነተኑ ፡
በኋላ ፤ እነዚህን ፡ ፍላጎቶች ፡ ለማሟላት ፡ ያስችላሉ ፡ ተብለው ፡ የሚገመቱት ፡ ሕጐች ፡
ምን ፡ ምን ፡ እንደሆኑ ፡ አስተያየት ፡ ይሰጣል ። ነገር ፡ ግን ፤ እነዚህ ፡ ወደፊት ፡
የሚወጡት ፡ ሕጐች ፡ ስለሚያመጡት ፡ ውጤት ፡ የሚደረገው ፡ ጥናት ፤ በሥራ ፡ ላይ፡
ስለዋሉ ፡ ሕጐች ፡ ከሚደረገው ፡ ተመሳሳይ ፡ ጥናት ፡ በኋላ ፡ ከሚሰጡት ፡ ወይም ፡
መደምደሚያዎች ፡ ይልቅ ፡ በይበልጥ ፡ አጠራጣሪ ፡ የሆኑ ፡ መደምደሚያ ፡ አስተያ
የቶች ፡ ሊያስከትል ፡ ይችላል ፤ ይህም ፡ የሚሆንበት ፡ ምክንያት ፡ ወደፊት ፡ ስለሚወ
ጣው ፡ ሕግ ፡ በሚደረገው ፡ ምርምር ፡ ውስጥ ፡ የሚተነተኑት ፡ በእርግጥ ፡ የሚታዩ ፡
ግንኙነቶች ፡ ሳይሆኑ ፡ በይበልጥ ፡ ልብ ፡ ወለድ ፡ የሆኑ ፡ ግንኙነቶች ፡ ስለሆኑ ፡ ነው ።
እንዲህም ፡ ሆኖ ፤ በሥራ ፡ ላይ ፡ የዋሉ ፡ ሕጐች ፡ ጥናትም ፡ ቢሆን ፤ የታሰቡትን ፡ ማሻ
ሻያ ፡ ወይም ፡ መሻሪያ ፡ ሕጐች ፡ አስፈላጊነትና ፡ የሚያስከትሉትንም ፡ ውጤት ፡
ጥናት ፡ ስለሚያጠቃልል ፤ አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ አጠራጣሪ ፡ ሆኖ ፡ ተገኝቷል ።

ይህ ፡ ሁሉ ፡ ረቂቅ ፡ ንግግር ፡ እነዚህ ፡ አስተያየቶች ፡ ሊያስተዋውቁ ፡ ካቀዳ
ቸው ፡ ሦስት ፡ ጥናቶች ፡ ጋር ፡ ያለው ፡ ግንኙነት ፡ ምንድን ፡ ነው ? ባጭሩ ፡ ይህ ፡ ነው፡-
ፕሮፌሰር ፡ ቤክስትሮምና ፡ ተባባሪዎቻቸው ፡ የአንዳንድ ፡ ጠቃሚ ፡ የኢትዮጵያን ፡
ሕጐችና ፡ የሕግ ፡ ድርጅቶች ፡ ውጤት ፡ በግል ፡ ስሜት ፡ ብቻ ፡ ላይ ፡ ባልተመሠረተ ፡
አኳኋን ፡ በማጥናት ፡ አስተያየት ፡ ለመስጠት ፡ ሞክረዋል ። እንደ ፡ ብዙዎቹ ፡ የሕግ ፡
ምሁራን ፡ ሕጉ ፡ በሚለው ፡ ወይም ፡ አንድ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ወይም ፡ አስተያየት ፡
ሰጭ ፡ በሰጠው ፡ ትርጉም ፡ ሳይወሰኑ ፤ ሕጐችና ፡ የሕግ ፡ ድርጅቶች ፡ በእርግጥ ፡ እን
ዴት ፡ እንደሚሰሩ ፡ ለመግለጽ ፡ ጥረዋል ። ይህም ፡ በእኔ ፡ አስተያየት ፡ ይበልጥ ፡
አስቸጋሪ ፡ ከመሆኑም ፡ በላይ ፤ አንድን ፡ ጽሑፍ ፡ አጠቃሎ ፡ ወይም ፡ ተንትኖ ፡ ከማ
ቅረብ ፡ ይበልጥ ፡ ጠቃሚነት ፡ ያለው ፡ ጉዳይ ፡ ነው ። ይህንም ፡ ለማድረግ ፡ ፕሮፌስ
ሩና ፡ ተባባሪዎቻቸው ፡ ከገዳም ፡ ኑሮ ፡ ጋር ፡ ተመሳሳይ ፡ ከሆነው ፡ የአካዳሚክ ፡
ክፍል ፡ ወጥተው ፡ በግልጽ ፡ ወደሚታየው ፡ የዛሬይቱ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ዓለም ፡ ገብተ
ዋል ። የሕጉን ፡ ጥቅምም ፡ የሆነ ፡ ጉዳት ፡ ለማወቅ ፡ የመጨረሻ ፡ የሚያስችለውን ፡
የሕጉን ፡ አሠራር ፡ በሚገባ ፡ አጥንተውታል ።

ፕሮፌሰር ፡ ቤክስትሮም ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ከመምጣታቸው ፡ በፊት ፤ አንዳ
ንድ ፡ የውጭ ፡ ዜጋ ፡ የሆኑ ፡ የሥራ ፡ ጓደኞቹ ፤ ፕሮፌሰሩ ፡ ያቀዱት ፡ ዓይነት ፡ የሕግ ፡
ምርምር ፤ በታዳጊ ፡ ሀገሮች ፡ ውስጥ ፡ ውጤት ፡ በሚሰጥ ፡ አኳኋን ፡ ሊደረግ ፡ እንዳል
ተቻለ ፡ ነግረውኝ ፡ ነበር ። የሚሰጧቸውም ፡ ምክንያቶች ፤ የሕግ ፡ ምሁራን ፡ የአጠናኑን፡
ዘዴ ፡ ስለማያውቁ ፤ ዘዴዎቹን ፡ ቢያጠኑም ፡ እንኳ ፡ ስለኅብረሰቡ ፡ በቂ ፡ ዕውቀት ፡
ከማጣታቸው ፡ በላይ ፤ ከቀበሌው ፡ ቋንቋዎች ፡ ጋር ፡ ያልተላመዱ ፡ ስለሆኑ ፤ ለመጀ
መር ፡ የሚያስችሉ ፡ መሠረታዊ ፡ ጥናቶች ፡ ስላልተደረጉ ፤ ጥናቶቹን ፡ በገንዘብ ፡ የሚ
ረዳ ፡ ማንም ፡ ባለመገኘቱ ፤ መረጃ ፡ ሰጪዎች ፡ ለመናገር ፡ ፈቃደኛ ፡ ባለመሆናቸውና፡
ውጤቶቹንም ፡ ማሳተም ፡ ስለማይቻል ፡ ነው ፤ የሚሉ ፡ ናቸው ። ስለዚህም ፤ በዚህ ፡
ፋንታ ፡ ሌላ ፡ ጽሑፍን ፡ በዝርዝር ፡ አጥንቶ ፡ በዚህ ፡ ላይ ፡ ማብራሪያ ፡ ማዘጋጀቱ ፡
አይሻልም ፡ ወይ ? ይላሉ ። ዳሩ ፡ ግን ፤ በዚህ ፡ መግቢያ ፡ በተገለጸው ፡ ጥናት ፡ ላይ ፡
የተሣተፉት ፡ ዋነኞቹ ፡ ሶስቱ ፡ ደራሲያንና ፡ በርካታውን ፡ የውጭውን ፡ ጥናት ፡ ያከና
ወኑት ፡ ሰላሳዎቹ ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ የሕግ ፡ ተማሪዎች ፤ እነዚህ ፡ ተጠራጣሪዎች ፡
መሳሳታቸውን ፡ ለማረጋገጥ ፡ መቻላቸውን ፡ አምንበታለሁ ። የጠቃሚ ፡ ሕጐችና ፡
የሕግ ፡ ድርጅቶች ፡ ውጤት ፡ ተጠንቶ ፤ ከፍተኛ ፡ ጭብጦች ፡ ተመርምረው ፤ የፍሬ ፡
ነገሮች ፡ ዝርዝርም ፡ በብዛት ፡ ተከማችቶ ፤ እውቀት ፡ ያላቸው ፡ ኢትዮጵያውያን ፡
ተባብረውበት ፤ ጥናቱ ፡ በመታተም ፡ ላይ ፡ ይገኛል ።

የእነዚህ ፡ ጥናቶች ፡ በቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ዩኒቨርሲቲ ፡ ውስጥ ፡ መከናወን ፡ የሚያስገርም ፡ አይደለም ። ነፃ ፡ የሆነና ፡ ፍሬ ፡ ያለው ፡ ምርምር ፡ የማድረጉ ፡ መንፈስ ፡ ከዩኒቨርሲቲው ፡ ጋር ፡ የተዋሃዱና ፤ ስለ ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ ችግሮችም ፡ በግል ፡ ስሜት ፡ ላይ ፡ ብቻ ፡ ያልተመሠረተ ፡ ጥናት ፡ የማድረግ ፡ ኃላፊነት ፤ በዓለም ፡ ያሉ ፡ ዩኒቨርሲቲዎች ፡ እንደተደናቂ ፡ ባሕል ፡ ይዘውት ፡ እንደቆዩ ፡ ሁሉ ፤ ከዩኒቨርሲቲው ፡ በይበልጥ ፡ የሚጠበቅ ፡ መሆኑን ፡ ወደኢትዮጵያ ፡ እንደመጣሁ ፡ በአጭር ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ለመረዳት ፡ ችዬ ፡ ነበር ። እነዚህ ፡ ጥናቶች ፡ ወደፊት ፡ ለሚደረጉ ፡ ተመሳሳይ ፡ ጥናቶች ፡ መሪ ፡ ይሆናሉ ፡ ብዬ ፡ ተስፋ ፡ አደርጋለሁ ። በተጨማሪም ፤ ኢትዮጵያውያን ፡ የሙሉ ፡ ጊዜ ፡ መምህራን ፡ በሚሆኑበት ፡ ጊዜ ፡ እነዚህን ፡ መሰል ፡ ጥናቶች ፡ እንደሚመሩ ፡ ተስፋ ፡ አደርጋለሁ ። በጥናቱ ፤ የተሳተፉት ፡ ተማሪዎች ፡ ያሳዩት ፡ ከፍተኛ ፡ የሥራ ፡ ውጤት ፤ በሕግ ፡ ትምህርት ፡ የሰለጠኑ ፡ ኢትዮጵያውያን ከትምህርት ፡ ቤት ፡ ውጭ ፡ ምርምር ፡ በማድረግ ፡ ረገድ ፡ የተለየ ፡ ችሎታ ፡ እንዳላቸው ፡ ያሳያል ።

የዩኒቨርሲቲው ፡ የሶሽያል ፡ ሳይንስ ፡ ክፍል ፡ እያደገ ፡ ሲሄድ ፤ የውጤት ፡ ምርመራ ፡ ዘዴ ፡ በሕጉ ፡ ፋክልቲ ፤ ሶሽያል ፡ ሳይንሱ ፡ ክፍልና ፡ በአስተዳደር ፡ ትምህርት ፡ ቤቶች ፡ ኅብረት ፡ ቢከናወን ፡ የጋራ ፡ ጥቅምን ፡ የሚያስገኝ ፡ ይሆናል ። እያንዳንዱ ፡ ወገን ፡ ከሌላው ፡ የሚማረው ፡ አንዳንድ ፡ ነገር ፡ ስላለና ፡ መተባበርም ፡ ስለኢትዮጵያ ፡ የሚደረገውን ፡ የእውቀት ፡ ቅንጅታዊ ፡ ክምችት ፡ ስለሚያፋጥነው ፤ ዩኑቨርሲቲው ፡ ለሀገሪቱ ፡ መፈጸም ፡ ያለበትን ፡ ምርምር ፡ የማድረግ ፡ ግዳጁን ፡ እግብ ፡ ማድረስ ፡ የዚህ ፡ ዓይነቱ ፡ ትብብር ፡ አስፈላጊ ፡ ይሆናል ። ደግሞ ፤ በአሁኑ ፡ ጊዜ ፡ ለሕግ ፡ ፋኩልቲውም ፡ ሆነ ፡ ለሌሎቹ ፡ የዩኒቨርሲቲው ፡ ፋኩልቲዎች ፡ በጣም ፡ አስፈላጊ ፡ የሆኑ ፤ ስለኢትዮጵያ ፡ መንግሥትና ፡ ስለኅብረተ ፡ ሰቡ ፡ ቁጥጥር ፡ አዲስና ፡ የተስፋፉ ትምህርቶች ፡ እንዲሰጡ ፡ ለማድረግ ፡ የሚያስችሉ ፡ የመማሪያ ፡ ጽሑፎችን ፡ ለማዘጋጀት ፡ የኅብረት ፡ የምርምር ፡ ፕሮግራሞች ፡ እንዲኖሩ ፡ ያስፈልጋል ። ምናልባትም፤ የኅብረት ፡ ምርምር ፡ የማድረጉ ፡ ጥረት ፡ ተማሪዎችን ፡ በማደባለቅና ፡ ከልዩ ፡ ልዩዎቹ ፡ የዩኒቨርሲቲው ፡ ክፍሎች ፡ ከሕጉ ፡ ክፍልም ፡ ጭምር ፡ የተውጣጡ ፡ መምህራንን ፡ በመጨመር ፡ እውነተኛ ፡ የሆኑ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ትምህርቶችን ፡ የሚያጠቃልሉ ፡ ትምህርቶችን ፡ ከመስጠት ፡ ከመርዳቱም ፡ በላይ ፡ የዩኒቨርሲቲው ፡ ከፍተኛ ፡ ባለሥልጣኖች ፡ ዘንድ ፡ በወረት ፡ ተደጋግሞ ፡ የሚወራው ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ትምህርቶችን ፡ የሚያጠቃልል ፡ የትምህርት ፡ አሰጣጥ ፡ የመፍጠር ፡ ሐሳብ ፡ ቁም ፡ ነገር ፡ ያዘለ ፡ እንዲሆን ፡ ለማድረግ ፡ ይረዳል ።

ምርምር ፡ ገንዘብን ፡ የሚጠይቅ ፡ ጉዳይ ፡ ነው ። ስለሆነም ፤ ምንም ፡ እንኳ ፡ ገንዘብ ፡ ለጥሩ ፡ ውጤት ፡ ዋስትና ፡ ባይሆንም ፡ ለምርምሩ ፡ ጥረት ፡ ግድ ፡ አስፈላጊ ፡ ነገር ፡ ነው ። የቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ዩኒቨርሲቲ ፡ በኖርዝዌስተርን ፡ ዩኒቨርሲቲ ፡ ለሚገኘው ፡ ካውንስል ፡ ፎር ፡ ኢንተርሶሳይታል ፡ ስተዲስ ፤ በተለይም ፡ የዚሁ ፡ ዲሬክተር ፡ ለሆኑት ፡ ለፕሮፌሰር ፡ ሪቻርድ ፡ ዲ ፡ ሽዋርትዝ ፤ በፕሮፌሰር ፡ ቤክስትሮምና ፡ በተባባሪዎቻቸው ፡ አማካይነት ፡ ለተደረገው ፡ ጥናት ፡ ማካሄጃ ፡ ስለሰጡት ፡ ገንዘብ ፡ ባለውለታ ፡ ነው ። የቀ/ኃ/ሥ/ ዩኒቨርሲቲ ፡ የሕግ ፡ ፋክልቲ ፡ ወደፊት ፡ ለሚያደርጋቸው ፡ ተመሳሳይ ፡ የምርምር ፡ ፕሮጀክቶች ፡ እርዳታ ፡ የሚውል ፡ ገንዘብ ፡ ሌሎች ፡ የእርዳታ ፡ ድርጅቶችም ፡ እንደሚለግሱ ፡ ተስፋ ፡ እናደርጋለን ።